


## መግቢያ

እንስታዊት በይነ መረብ (ፌሚኒስት ኢንተርኔት) በርካታ ሴቶችን ለማብቃት፤ እንዲሁም በብዝኃነት በሁሉም ልዩነቶቻችን ውስጥ - መብቶቻችንን ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም፣ ደስታን ለማግኘትና እና በወንድ አምሳል የተቀረፀውን አባታዊ ሥርዓትን ለማስወገድ ይሰራል። ይህ ያለፍንበትን የተለያየ ነባራዊ ሁኔታ ማለትም ዕድሜን፣ የአካል ጉዳትን፣ ፆታን፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን፣ ፖለቲካዊና ሀይማኖታዊ እምነቶችን፣ የጎሳ አመጣጥ እና የዘር መለያዎችን ጨምሮ የተለያዩ ክፍፍሎችን፣ እውነታ፣ አውድ እና ዝርዝር ጉዳዮችን ያጠቃልላል።

የፊሚኒስት በይነመረብን ዕውን ለማድረግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቁልፍ መርሆች ወሳኝ ናቸው።

## ተደራሽነት

### 1. የበይነ መረብ ተደራሽነት (Access to the internet)

እንስታዊት በይነ መረብ በርካታ ሴቶችን አለምአቀፋዊ፣ ቅቡል ፣ አቅምን ያገናዘበ፣ ጥራቱን የጠበቀ፣ በምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ፣ ትርጉም ያለው ፣ለሁሉም ክፍትና እኩል የሆነ የበይነ መረብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ወይም አገልግሎቱን እንዲያገኙ ተደራሽ ከማድረግ ይጀምራል።

### 2. የመረጃ ተደራሽነት (Access to information)

ሴቶች የሚመለከቷቸው ጉዳዮች ላይ መረጃ የማግኘት ያልተገደበ መብት እንዲኖራቸው እንደግፋለን፤ በተለይም የሥነ ተዋልዶ ጤናና ጤናማ የወሲብ ህይወትን የሚመለከቱ መረጃዎች፣ ጥንቁቅ ፅንስ ማቋረጥን፣ ፍትህ የማግኘት መብት፣ የወሲብ ምርጫ እና ተያያዥ ጉዳዮችን በሚመለከት መረጃ ሊያገኙ ይገባል። ይህም በቋንቋዎች፣ በአካላዊ ችሎታዎች ወይም አለመቻሎች፣ በፍላጎቶች እና አውዶች (contexts) ውስጥ ያሉ ልዩነቶችን የሚያጠቃልል ነው።

### 3. **የቴክኖሎጂ አጠቃቀም** (Usage of technology)

ሴቶች የመረጃ እና ግንኙነት ቴክኖሎጂዎችን የኮምፒውተር ቋንቋ ፕሮግራም የመንደፍ (Coding)፣ ዲዛይን የማድረግ፣ የማላመድ ፣ በጥልቀትና በዘላቂነት የመጠቀም እና ቴክኖሎጂን የፈጠራና ሀሳብን የመግለጫ እንዲሁም በሁሉም ቦታዎች ያሉ የፆተኝነትና ፆታን መሠረት ያደረጉ አድልኦዎችን የሚያበረታቱ ልማድና ባህሎችን የመሞገቻ መድረክ አድርጎ የመጠቀም መብት አላቸው።




## ንቅናቄዎችና ህዝባዊ ተሳትፎ

### 4. **ትግል** (Resistance)

በይነ መረብ ማህበራዊ ዕሴቶች የሚተወኑበት፣ የሚፀኑበትና የሚጫኑበት መድረክ እንዲሁም በወንዶች እይታ የተቀረፁ ሌሎች አደባባዮችና መድረኮች ተቀጥላ ነው:: ለእንስታዊት በይነ-መረብ የምናደርገው ትግል በሌሎች ቦታዎች፣ በአደባባይ በግል እና በሁለቱ መካከል ባሉ መድረኮች ሁሉ ላይ የምናደርጋቸው ትግሎች አንዱ አካል ነው።

### 5. **የንቅናቄ ግንባታ** (Movement building)

በይነ መረብ ትልቅ ለውጥ የሚያመጣ ፖለቲካዊ መድረክ ነው። ግለሰቦች ማንነታቸውን እና ፆታቸውን የሚመለከቱ እውነታዎችን እንዲያውቁ እንዲገነቡ እንዲመረምሩ ያግዛቸዋል። ይህ ደግሞ አገራትና ሉዓላዊ ግዛቶችን ተሻግሮ ግንኙነት መመሥረትን ተጠያቂነትና ግልጽነትን መሻትና ዘላቂነት ያለው እንስታዊ ንቅናቄ እንዲፈጠር እድል መፍጠርን ያጠቃልላል።

### 6. **የበይነ-መረብ አስተዳደር** (Internet governance)

በወንዶች አንፃር የተቃኙ የበይነ መረብ አስተዳደርን የሚቆጣጠሩ ከባቢዎችና ሂደቶችን በመሞገት እናምናለን። ሴቶችንና የእንስታዊነት አራማጆችን ወደ ውሳኔ ሰጪነት በማምጣትም እንዲሁ። በይነ መረብን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች አወጣጥ ሂደት ዲሞክራሲያዊ እንዲሆንና ባለቤትና ሥልጣን ከአለማቀፋዊ ወደ አካባቢያዊ እንዲዛወር እንሻለን::

## ኢኮኖሚ

### 7. አማራጭ ኢኮኖሚዎች (Alternative economies)

ቴክኖሎጂን በትርፍ ላይ የተመሰረተና በይበልጥ ጥቂት ትልልቅ የግል ድርጅቶች ብቻ የሚቆጣጠሩት ወደመሆን የሚገፋውን የካፒታሊስት (ከበርቴያዊ) አሠራር ለመመርመር ዝግጁ ነን። በትብብር፣ በአብሮነት ፣ በጋራ ፣ በአካባቢያዊ ዘላቂነት እና በግልፅነት መርሆዎች ላይ የተመሰረቱ አማራጭ የኢኮኖሚ ኃይል ዓይነቶችን ለመፍጠር እንሰራለን ።

### 8. ነፃ እና ክፍት ምንጭ (Free and open source)

የዲጂታል ደህንነት እና ጥበቃን ጨምሮ በቴክኖሎጂ ፈጠራና ሙከራዎችን ለማድረግ እንዲሁም ነፃ እና ክፍት ምንጭ ሶፍትዌሮችን (FLOSS) ፣ መሣሪያዎችን እና መድረኮችን ለመጠቀም ቁርጠኞች ነን። ስለ ነፃ እና ክፍት ምንጭ ሶፍትዌሮች (FLOSS) አጠቃቀም ማስተዋወቅ ፣ ማሰራጨት እና ማጋራት የሥራችን አንዱ አካል ነው።



## ሐሳብን መግለፅ

### 9. የእንስታዊነት ተዋስኦ ማጉላት (Amplifying feminist discourse)

የሴቶችን ተረክ እና የኑሮ ልምዶች በማጉላት ረገድ የበይነ-መረብን አስተዋፅዎ መጠቀም ይገባናል። የሴቶችን ድምፅ በማፈንና እና ሴት የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን በማሳደድ ድምፃችን በብቸኛ የበላይነት የሚቆጣጠሩ የመንግስት፣ የሃይማኖት መብት እና ሌሎች ፅንፈኛ ኃይሎችን እንቃወማለን ።

### 10. ሀሳብን በነፃነት መግለፅ (Freedom of expression)

የሴቶች (በፆታ ላይ የተመሰረተ) ራስን የመግለጽ መብት ፖለቲካዊ አልያም እምነትን የሚመለከቱ ሃሳቦችን ከመግለጽ የሚያንስ መብት አለመሆኑን መግለጽ እንፈልጋለን። መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት/ተዋንያን ቴክኖሎጂን፣ ህግ ማውጣትን እና የነውጥ ኃይልን በመጠቀም በይነመረብ የፆታ እኩልነት ተሟጋቾችን ሀሳብና ድምፃችን ለመቆጣጠር፣ ለመሰለል እና ለመገደብ የሚያደርጉትን ጥረት በጥብቅ እንቃወማለን። ይህንን የሞራል ፖሊሲ ፣ ሳንሱር እና የዜግነት እና የመብቶች ተዋረድ ትልቁ የፖለቲካ ፕሮጀክት አካል እንደሆነ እንገነዘባለን ።

### 11. የወሲብ ፊልሞች እና "ጎጂ ይዘት" (Pornography and “harmful content”)

በበይነ-መረብ ላይ ፀያፍ የሆኑ ወሲብ ነክ ምስሎች ጉዳይ ከውክልና ፣ ከፈቃደኝነት ፣ ከስልጣን እና ከጉልበት ጋር የተቆራኘ መሆኑን እንገነዘባለን ። በእነዚህ ምስሎች ይዘት እና በሴቶች ላይ በሚፈፀም ጥቃት መካከል የሚደረጉ ቀላል የምክንያት ትስስርን አንቀበልም። እንዲሁም “ጎጂ ይዘት” የሚለውን የጅምላ ቃል የሴቶችን ፆታዊነት ለመግለፅ መጠቀምን አንቀበልም። ጤናማ የሆነ ፆታዊ ራስን መግለፅን እንደግፋለን።

### 12. ነፃ ፈቃድ (Consent)

በበይነ-መረብ ባህል ፣ ዲዛይን ፣ ፖሊሲዎች እና የአገልግሎት ውሎች ውስጥ የነፃ ፈቃድ ሥነ ምግባርንና አሠራርን መገንባት አስፈላጊ እንደሆነ በማመን ተግባራዊ እንዲሆን እንሞግታለን። ሴቶች በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ግላዊም ሆነ ግልፅ የሆነ የህይወታቸውን ገፅታ ለማጋራት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ የማድረግ ችሎታቸው የሴቶችን የሰውነት ክብር የሚገልፅ ነው።




**13. ግላዊ ምሥጢርና ውሂብ (Privacy and Data)**

በበይነ መረብ ላይ የሚገኙ መረጃዎች የግል ምስጢር መሆናቸውንና እነዚህንም ሙሉ በሙሉ የመቆጣጠር መብት መከበርን በሁሉም ደረጃ እንደግፋለን። መረጃዎችን ለትርፍ ለመጠቀም እና በበይነመረብ ላይ ባህሪን ለመቆጣጠር በመንግስት እና በግል ኩባንያዎች የሚደረጉ ልማዶችን እንቃወማለን። ክትትል/ስለላ የሴቶች አካልን ፣ ንግግርን እና የመብት ተሟጋችነትን (አክቲቪዝም) ለመቆጣጠር እና ለመገደብ የሚያገለግል የአባታዊው ሥርዓት ታሪካዊ ሥልት ነው:: በግለሰቦች ፣ በግሉ ዘርፍ ፣ በመንግስታዊና እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተዋንያን ለሚደረጉ የክትትል ተግባራትም እኩል አትኩሮትን እንሰጣለን ።

**14. ማህደረ ትውስታ (Memory)**

በኢንተርኔት ግለ-ታሪካችንን እና ማህደረ ትውስታችንን የመቆጣጠርና ያንንም ተግባራዊ የማድረግ መብት አለን። ይህ ሁሉንም የግል ውሂቦቻችንና እና መረጃዎቻችንን በበይነ መረብ ላይ ማግኘት መቻልን፣ ማን ማግኘት እንደሚችል እና በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ማወቅ እና እስከመጨረሻው የመሰረዝ ችሎታን ጨምሮ በእነዚህ መረጃ ላይ ሙሉ ቁጥጥር ማድረግ መቻልን ያጠቃልላል ።

**15. ስውር ሥም (Anonymity)**

በበይነ መረብ እንቅስቃሴዎች ላይ ማንነትን ያለማሳወቅና ስውር ሥም የመጠቀም መብትን እንደግፋለን፤ ማንነትን አለማሳወቅን የሚገድብ ሁሉንም ጥያቄ ውድቅ እናደርጋለን። ማንነት እንዳይታወቅ ማድረግ በይነመረብ ላይ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ ነፃነትን ያጎናፅፋል ፣በተለይም በፆታዊ አድልዎ ለተጠቁ ሴቶች ተጨማሪ ጥቃት ዒላማ እንዳይሆኑ ደህንነት ለማረጋገጥ ያስችላል።

**16. ህፃናትና ወጣቶች (Children and youth)**

በበይነመረብ ላይ የሚደረጉ የጥበቃ እና ደህንነት ውሳኔዎች ውስጥ የወጣቶች ድምፅ እና ልምዶችና ምልከታዎች እንዲካተቱ እንዲሁም ደህንነታቸውን፣ ግላዊነታቸውን እና የመረጃ ተደራሽነታቸውን እንዲያሳድጉ ጥሪ እናቀርባለን። የልጆችን ጤናማ ስሜታዊ እና ፆታዊ ዕድገት የማግኘት መብትን እንገነዘባለን:: ይህም የግላዊነት መብትን እና በሕይወታቸው ውስጥ ወሳኝ በሆኑ ጊዜያት ስለ ፆታና ስነ-ጾታዊ ጉዳዮች አዎንታዊ መረጃ የማግኘት መብታቸውን ያጠቃልላል ።

## 17. **የበይነ-መረብ ጥቃት (Online violence)**

የበይነመረብ ተጠቃሚዎች ፣ የፖሊሲ አውጪዎች እና የግሉን ዘርፍ ጨምሮ ሁሉም የኢንተርኔት ባለድርሻ አካላት በበይነመረብ የሚደርሱ ትንኮሳ እና ከቴክኖሎጂ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጥቃቶችን ለማስወገድ ትኩረት ሰጥተው እንዲሠሩ እንጠይቃለን።
በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች ፣ ዛቻዎች ፣ ማስፈራሪያዎች እና ቁጥጥሮች በእውን የሚታዩ ፣ ጎጂ እና አሳሳቢ ናቸው ፤ እናም ሰፋ ያለው በጾታ ላይ የተመሠረተ ጥቃት አንዱ አካል ናቸው። ይህንን መፍታትና ማስቆም የጋራ ሀላፊነታችን ነው።